ONE VOICE
FELLOWSHIP

# Worship Service

**March 28, 2021**

## Welcome

**Clément Tendo**

## Call to Worship | Psalm 118: 15-29

**Kevin & May Faulkner** | *English & Chinese*

**Psalm 118:15-29**

15 在义人的帐棚里，
有欢呼和得胜的声音，说：
*(Glad songs of salvation
are in the tents of the righteous:)*

**"The right hand of the Lord does valiantly,**

16 **the right hand of the Lord exalts,
the right hand of the Lord does valiantly!"**

17 我必不至于死，我要活下去，
并且要述说耶和华的作为。
*(I shall not die, but I shall live,
and recount the deeds of the Lord.)*

18 **The Lord has disciplined me severely,
but he has not given me over to death.**

19 请你们为我打开正义的门，
*(Open to me the gates of righteousness,)*

**that I may enter through them
and give thanks to the Lord.**

20 这是耶和华的门，
义人才可以进去。
*(This is the gate of the Lord;
the righteous shall enter through it.)*

21 **I thank you that you have answered me
and have become my salvation.**

22 建筑工人所弃的石头，
成了房角的主要石头；
*(The stone that the builders rejected
has become the cornerstone.)*

23 **This is the Lord's doing;
it is marvelous in our eyes.**

24 这是耶和华所定的日子，
*(This is the day that the Lord has made;)*

**let us rejoice and be glad in it.**

25 耶和华啊！求你施行拯救；
耶和华啊！求你使我们亨通。
*(Save us, we pray, O Lord!
O Lord, we pray, give us success!)*

26 **Blessed is he who comes in the name of the Lord!
We bless you from the house of the Lord.**

27 耶和华是　神，
他光照了我们。
*(The Lord is God,
and he has made his light to shine upon us.)*

**Bind the festal sacrifice with cords,
up to the horns of the altar!**

28 你是我的　神，我要称谢你；
你是我的　神，我要尊崇你。
*(You are my God, and I will give thanks to you;
you are my God; I will extol you.)*

29 **Oh give thanks to the Lord, for he is good;
for his steadfast love endures forever!**

## Song of Praise | Hosanna

**Praise team** | *English*

I see the King of glory
Coming on the clouds with fire
The whole earth shakes
The whole earth shakes

I see His love and mercy
Washing over all our sin
The people sing
The people sing

***Chorus***
Hosanna Hosanna

Hosanna in the highest
Hosanna Hosanna
Hosanna in the highest

I see a generation
Rising up to take their place
With selfless faith
With selfless faith

I see a near revival
Stirring as we pray and seek
We're on our knees
We're on our knees

***Bridge***
Heal our hearts and make them clean
Open up our eyes to the things unseen
Show us how to love
Like You have loved us

Break our heart for what breaks Yours
Everything we are
For Your kingdom's cause
As we walk from earth into eternity

***Chorus***
Hosanna Hosanna
Hosanna in the highest
Hosanna Hosanna
Hosanna in the highest

## Song of Praise | Hosanna (Hosanna in the Highest)

**Praise team** | *English*

Hosanna, Hosanna, hosanna in the highest
Lord we lift up your name
With our hearts full of praise
Be exalted O Lord our God
Hosanna in the highest

Sing glory, sing glory sing glory to the King of kings
Lord we lift up your name
With our hearts full of praise
Be exalted O Lord our God
Hosanna in the highest

## Opening Prayer

**Abrham** | *English & Amharic*

## Scripture Reading | Matthew 21:1-11

**Kebron & Nebiat** | *Amharic*

**ማቴዎስ 21: 1-11**

1 ወደ ኢየሩሳሌምም ቀርበው ወደ ደብረ ዘይት ወደ ቤተ ፋጌ ሲደርሱ፥
ያንጊዜ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ሁለት ላከ፥

2 እንዲህም አላቸው። በፊታችሁ ወዳለችው መንደር ሂዱ፥ በዚያን ጊዜም
የታሰረችን አህያ ውርንጫም ከእርስዋ ጋር ታገኛላችሁ፤ ፈትታችሁ
አምጡልኝ።

3 ማንም አንዳች ቢላችሁ። ለጌታ ያስፈልጉታል በሉ፤ ወዲያውም
ይሰዳቸዋል።

5 ለጽዮን ልጅ። እነሆ፥ ንጉሥሽ የዋህ ሆኖ በአህያ ላይና በአህያይቱ ግልገል
በውርንጫይቱ ላይ ተቀምጦ ወደ አንቺ ይመጣል በሉአት ተብሎ በነቢይ
የተነገረው ይፈጸም ዘንድ ይህ ሆነ።

6 ደቀ መዛሙርቱም ሄደው ኢየሱስ እንዳዘዛቸው አደረጉ፥

7 አህያይቱንና ውርንጫዋንም አመጡለት፥ ልብሳቸውንም በእነርሱ ላይ
ጫኑ፥ ተቀመጠባቸውም።

8 ከሕዝቡም እጅግ ብዙዎች ልብሳቸውን በመንገድ ላይ አነጠፉ፥
ሌሎችም ከዛፍ ጫፍ ጫፋን እየቈረጡ በመንገድ ላይ ያነጥፉ ነበር።

9 የሚቀድሙትም ሕዝብ የሚከተሉትም። ሆሣዕና ለዳዊት ልጅ በጌታ
ስም የሚመጣ የተባረከ ነው፤ ሆሣዕና በአርያም እያሉ ይጮኹ ነበር።

10 ወደ ኢየሩሳሌምም በገባ ጊዜ መላው ከተማ። ይህ ማን ነው? ብሎ
ተናወጠ።

11 ሕዝቡም። ይህ ከገሊላ ናዝሬት የመጣ ነቢዩ ኢየሱስ ነው አሉ።

## Membership Vows

**All**

## Prayer | Our Father

**All**

**ማቴዎስ 6: 9-13**

9 ስምህ ይቀደስ፤ መንግሥትህ ትምጣ፤ ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች
እንዲሁ በምድር ትሁን፤

10 የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን፤

11 እኛም ደግሞ የበደሉንን ይቅር እንደምንል በደላችንን ይቅር በለን፤

12 ከክፉም አድነን እንጂ ወደ ፈተና አታግባን፤ መንግሥት ያንተ ናትና ኃይልም ክብርም ለዘለዓለሙ፤ አሜን።

13 ለሰዎች ኃጢአታቸውን ይቅር ብትሉ፥ የሰማዩ አባታችሁ እናንተን ደግሞ ይቅር ይላችኋልና፤

## Baptism

## Song of Praise | Yesu Azali Awa

**Praise team** | *Swahili, Spanish, & English*

***[Swahili]***
Yesu azali awa
Yesu azali awa
Yesu azali awa na biso

Alleluia, O Alleluia, Alleluia na Yesu!

***[Spanish]***
Jesucristo está aquí
Jesucristo está aquí
Jesucristo está en este lugar

Aleluya, Oh Aleluya, Aleluya a Jesús

***[Spanish]***
Jesus Christ is here with us
Jesus Christ is here with us
Jesus Christ is here with us, He is here

Alleluia, O Alleluia, Alleluia... He is here

***[Swahili]***
Yesu azali awa
Yesu azali awa
Yesu azali awa na biso

Alleluia, O Alleluia, Alleluia na Yesu!

**Leader: Louez Louez Louez**
All: Amen, Alleluia

**Leader: Louez Louez Louez**
All: Amen, Alleluia

**Leader: Louez Louez Louez**
All: Amen, Alleluia

## Song of Praise | Jalali Yesu

**You are full of grace & truth** *(men)*
You are full of grace & truth *(ladies)*
**Jalali Yesu** *(men)*
Jalali Yesu *(ladies)*

***Chorus***
**Jalali Yesu** *(men)*
Jalali Yesu *(ladies)*

***[Spanish]***
**Grande y bueno eres tú** *(men)*
Grande y bueno eres tú *(ladies)*

**Glorioso Cristo** *(men)*
Glorioso Cristo *(ladies)*

***Bridge*** *(All)*
You are glorious
Over all the earth (3x)
You are glorious!

**You are making all things new** *(men)*
You are making all things new *(ladies)*
**Jalali Yesu** *(men)*
Jalali Yesu *(ladies)*

**Jalali Yesu** *(men)*
Jalali Yesu *(ladies)*

## Tithes & Offerings

**Clément Tendo**

## Sermon | Ephesians 4:1-8

**Clément Tendo** | *English*

The sermon will be in your language on page 5.

## Respond in Song | Digne/Digno/Worship

**Praise team** | *French, English & Spanish*

Tu es digne
You are worthy
Eres digno
Digno de recibir

Mi pasado
Mi futuro
Eres digno
Digno de recibir

***Chorus***
Toda la gloria
Toda la honra
Lord, You are worthy
*Lord, You are worthy, forever worthy!*
God

You are worthy
Eres digno
Tu es digne
Digne de recevoir

Tout mon bonheur
Toutes mes souffrances
Tu es digne
Digne de recevoir

***Bridge***
Lord you are worthy, forever worthy
Lord you are worthy, forever worthy
Lord you are worthy, forever worthy
God

***Chorus***
Toda la gloria
Toda la honra
Lord, You are worthy
*Lord, You are worthy, forever worthy!*
God

## Communion

**Chris Sicks** | *English*

**Who can participate in the Lord's Supper?**

The Lord's Supper is a sacrament—a holy interaction between God and His people. It celebrates the spiritual union that Christians have with Christ. It is also called communion, because it strengthens the community we share with every brother and sister who trust in Jesus alone for salvation.

God's Word warns us that "Whoever eats the bread or drinks the cup of the Lord in an unworthy manner will be guilty concerning the body and blood of the Lord." (1 Corinthians 11:27) We must think carefully about this sacrament. It is only for those who:

1. have examined their conscience,
2. who truly understand the nature of the body of Christ,
3. who have committed their entire life to following Him,
4. who are members of a bible-believing church.

**Before you come to the table you must first come to Jesus in faith!**

We are not to judge people's hearts. Ask the Holy Spirit to examine your heart. If you are not sure about your relationship with Christ, do not participate in the sacrament. Instead, please let us pray for you. We love you and want you to join our community! But first you must be joined to Christ. Our leaders are available to talk and pray with you, to help you on your journey.

*"If you confess with your mouth that Jesus is Lord and believe in your heart that God raised him from the dead, you will be saved. For with the heart one believes and is justified, and with the mouth one confesses and is saved."* (Romans 8:9-10)

## Communion Song | Tera Lahoo Say Pap

**Kashif** | *Urdu*

## Prayer of Thanks

**Mae Klinger** | *English*

## We Respond, Rejoice, and Reach | Our promise as a church

**Chris Sicks** | *English*

**ALL:** By the power of the Holy Spirit,
we live in harmony with our brothers and sisters in Christ's Body.
We worship and glorify God the Father together with one voice.
And we welcome our neighbors as Christ welcomed us, for the glory of God.

## Benediction

**Chris Sicks** | *English*

# መልዕክት
# አንድነት በክርስትና ጉዞ

የሚቀርብ መልዕክት: 2021 ማርች 28, እሑድ

በክሌመንት ቴንዶ

## እንጸለይ

አባት ሆይ በዛሬዉ ዕለት በምስጋና ወደፊትህ እንቀርባለን። ስለቃልህና ስለአንድ ድምጽ ሕብረት እናመስግንሃለን። በዛሬዉ ዕለት በቃልህ በኩል ድምጽህን ስለምንሰማ እናመሰግንሃለን። ለእኛ ስትናገር በምናደምጥህ ጊዜ ዓይኖቻችንና ጆሮአቻችንና ክፈት። በደስታ ምላሽ እንድንሰጥ እርዳን። ለሕዝብህ ስናገር መስማት የሚገባቸዉን ለማስተላለፍ እንደመሳሪያ ተጠቀመኝ። ይሄንንም በጌታ በኢየሱስ ታምነን እንፀልያለን፡ ፡

## አስተዋፅዖ

**1. የክርስቲያኖች እርምጃ**
**(ቁጥር 1-3)**

**11. የሕብረታችን መሠረት**
**(ቁጥር 4-6)**

**111. የአንድነታችን ስጦታ**
**(ቁጥር 7-8)**

**ኤፌሶን 4: 1-8**

እንግዲህ በጌታ እስር የሆንሁ እኔ በተጠራችሁበት መጠራታችሁ እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ እለምናችኋለሁ፣ በትሕትና ሁሉና በየዋህነት በትዕግስትም እርስ በርሳችሁ በፍቅር ታገሡ፣ በሠላም ማሰሪያ የመንፈስን ማሠሪያ የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ ትጉ። በመጠራታችሁ በአንድ ተስፋ እንደተጠራታችሁ አንድ አካልና አንድ መንፈስ አለ። አንድ ጌታ አንድ ሃይማኖት፣ አንዲት ጥምቀት፣ ከሁሉ በላይ የሚሆን በሁሉም የሚሠራ፣ በሁሉም የሚኖር፣ አንድ አምላክ የሁሉም አባት አለ። ነገር ግን እንደክርስቶስ ስጦታ መጠን ለእያንዳንዳችን ፀጋ ተሰጠን። ስለዚህ በወጣ ጊዜ ምርኮን ማረከ፣ ለሰዎችም ስጦታን ሰጠ።

## መግቢያ

ለተወሰ ጊዜ የኤፌሰን መጽሐፍን እየተመለከትን ነበር። በዚህ መጽሐፍ ጳዉሎስ ስለአስተምሮዉ ብቻ አይደለም እያወራ ያለዉ። እንዴት ልንኖረዉ እንደሚገባንም ነዉ እያወራ ያለዉ። በዘራችን እንዳልዳንን ይጽፍልናል። ነገር ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል ባለዉ እምነት ነዉ። ይህም በቃሉ ላይ ብቻ እንዳቀረበዉ አስተምሮና ለእግዚአብሔር ክብር ብቻ ነዉ።

ከየትኛዉም ክፍል ሁን በእምነት በሆነዉ በፀጋ ከክርስቶስ ጋር ሕብት በፈፀምህ ቅስበት የክርስቶስ አካል ትሆናለህ። በዚህ ክፍል ጳዉሎስ አንድነታችን በክርስቶስ ላይ እንደተመሠረተ እንድናዉቅ ይፈልጋል። እርሱም ከእርሱ ጋር በመተባበር አንድ አካል አድርጎናል። እንደእርሱ አካል በአንድ የጋራ እምነት፣ አንድ ጥምቀትና አንድ ተስፋ በአብሮነት እንካፈላለን ። በክርስትና ሕይወት እርምጃችን የመንፈስን አንድነት እንድንጠብቅ ተጠርተናል። የዛሬዉ ትኩረታችን በዚህ ላይ ነዉ።

## 1. የክርስቲያኖች እርምጃ
## (ቁጥር 1-3)

### የክርስያኖች እርምጃ አንድነትን ይጠብቃል። ቁጥር አንድን እንመልከት

1. የክርስቲያኑ ጥሪ የክርስቲያኑን እርምጃ ይቀድማል። ምክኒያቱም እንደድምጹ መራመድ የቻልነዉ በእግዚአብሔር ስለዳንን ነዉ። ከዚህ የተነሳ ነዉ ልንታዘዘዉ የቻልነዉ።

2. እንደአማኞች የትሕትናና የተረጋጋ ኑሮ እንመራለን።

የጥንቷ የሮማዊቷ ዓለም ለትሕትናና ለጭምትነት ዋጋ አትሰጥም ። ሰዉ ሁሉ ክብርን ይፈልጋል- ከዚህም የተነሳ ሰዎች ሌሎችን ዝቅ አድርገዉ ይመለከታሉ። በዚህ ቦታ ጳዉሎስ የኤፌሶንን ሰዎች ለራሳቸዉ ክብርን እንዳይፈልጉ ያስተምራቸዋል። ነገር ግን ለሌሎች አማኞች ሲባል ራሳቸዉን እንዲዋርዱ እንጂ። ከሌሎች ጋር በምናደርገዉ ምልልስ ጭምቶች የመሆን ጥሪ ተቀብለናል። ጨዋ የሚለዉ ቃል ጭምት በሚለዉ ቃል ሊተረጎም ይችላል።

ጭምት የሆነ ወንድ ወይም ሴት ሌላዉን ሰዉ አያስቆጣም ወይም አያስቀይምም፣ እርሱ ራሱም በቀላሉ አይቆጣም አይቀየምም። ወገኖች ይሄ ለእኔም ለእናንተም የተለመደ ነገር አይደለም። ከክርስትና ጥሪ ጋር ሰማያዊ እሴት ነዉ።

ለእዉነተኛ የትሕትና ሕይወትና ጭምትነት ክርስቶስ ጥሩ ምሳሌ ነዉ። በፍልጵስዩስ 2:5-11 የሚከተለዉን እናነባለን:

**ፊልጵስዩስ 2: 5-11**

በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረ ይህ ሃሳብ በእናንተ ዘንድ ደግሞ ይሁን። እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቆጠረዉም። ነገር ግን የባሪያን መልክ ይዞ በሰዉም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ። በምስሉም እንደሰዉ ተገኝቶ ራሱን አዋረደ ራሱን አዋረደ፣ ለሞትም ይኸዉም የመስቀል ሞት እንኳን የታዘዘ ሆነ። በዚህ ምክያት ደግሞ እግዚአብሔር ያለልክ ከፍ ከፍ አደረገዉ፣ ከስምም ሁሉ በላይ ያለዉን ስም ሰጠዉ። ይህም በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ መላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደሆነ ይመሰክር ዘንድ ነዉ።

ክርስቶስ ምንም እንኳን ኃጢአት የለሽ ቢሆንም በኃጢአተኞች መካከል ሊኖር መረጠ። እኛ የሚገባንን ሞት ሞተ። እንደዚያም ሆኖ በጭምትነት ሕይወቱን መራ። ሞትን በተጋፈጠበት ጊዜ እንኳን "አባት ሆይ የሚደርጉትን አያዉቁምና ይቅር በላቸዉ" ሲል ፀልዮአል (ሉቃስ 23፡34)። ይሄ በጣም ከባድ ነዉ፣ ነገር እንደዚያ እንድንሆንና ያንን እድናደርግ ነዉ የተጠራነዉ። ኢየሱስን የበለጠ ባወቃችሁ መጠን እርሱን የመመስል ዕድላችሁ የሰፋ ይሆናል።

በዚህ እርምጃ የረጅም ጊዜ ስቃይና መቻቻል አብረዉ ሊሄዱ ይገባል። ብዙ ጊዜ የተቸገረ ሰዉ ወይም ሴት ናት ሌሎችን መሸከም የምትችለዉ። እርስ በርሳችን ልንፈታተሽ የምንችልበት ዕድል ይኖራል። ምክኒያቱም ኃጢአተኞች የሚያደርጉት ያንን ነዉ። ነገር ግን ኢየሱስ ሲሰጥ ጭምትነት ይመጣል፣ ጭምት ለመሆን፣ ትግስተኛ ለመሆን፣ ይቅር ባይ፣ ደግና ጨዋ ለመሆን ኃይል እናገኛለን።

ባክ ሆም የተባለዉ ሰዉ "አብረዉ የሚግጡ ላሞች ናቸዉ ቀንዳቸዉ እርስ በርሱ የሚጋጨዉ"። በእርግጥ እኛ ላሞች አይደለንም ። ነገር ግን ኃጢአተኛ የሆኑ ሰዎች አንዳቸዉ በሌላዉ ጣት ላይ ይቆማል። ወገኖች እኛም አብረን እስካለን ድረስ አርስ በርሳችን መጎዳዳታችን አይቀርም። አንዳችን የሌላዉን ትዕግስት እንፈትናለን። ነገር ግን የጳዉሎስ፡ የእኛን ችግር የመሸከም ልብና ጭምትነት እንዲኖረን ጥሪ ያቀርብልናል።

ምሳሌ፡ እነሆ፡ ኒካራጉዋ ከሚባል ቦታ አንድ ሰዉ እንዲህ ሲል ተናገረ በሠርጉ እለት ወላጆቹ ከተወሰነዉ ሰዓት 45 ደቂቃ አሳልፈዉ መጡ። የእጮኛዉ ቤተሰብ የሆኑት ደግሞ (አሜሪካዊ ሰዎች ናቸዉ) ከተወሰነዉ ጊዜ 45 ደቂቃ ቀድመዉ መጡ። በጣም ወሳኝ በሆነዉ በሠርግህ ዕለት በዚህ ሁኔታ ዉስጥ እንዳለ ሰዉ ራስህን አስብ። አማቾችህ አርፍደዉ ቢመጡ ምን ይሰማሃል? እኔ በግሌ እጎዳለሁ። ነገር ግን እንደ ክርስቲያን ቻይ እንድንሆን ተጠርተናል።

ነገር ግን ቻይ መሆን በዉስጣችን መሞት ማለት አይደለም። ይሄ በአገር ቤት ሰዎች ሲጎዱ የሚሰማቸዉ ስሜት ነዉ። ነገር ግን ምንም እንዳልተሳናቸዉ ሰዎች እናስመስላለን። በዉስጣችን ለመሞት ስንመርጥ እንደግብዞቸች እንቆጠራለን። ግልጽ አይደለንም ያም ደግሞ በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአት ነዉ። ለጓደኞቻችን ሐቀኞች አንሆንም፣ በመጨረሻም ለእግዚአብሔር ሐቀኝነታችንን እናጓድላለን።

ከዚያ ይልቅ ጳዉሎስ እዉነትን በፍቅር እንድንናገር ጥሪ ያቀርብልናል። በኤፌሶን መጽሐፍ 4፡15-16 ላይ ጳዉሎስ እንዲህ ሲል ጽፏል፡

**ኤፌሶን 4: 15-16**

ነገር ግን እዉነትን በፍቅር እየያዝን በነገር ሁሉ ወደእርሱ ራስ ወደሚሆን ወደክርስቶስ እንደግ ከእርሱም የተነሳ አካል ሁሉ እያንዳንዱ ክፍል በልክ እንደሚሠራ በተሰጠለት በጅማት ሁሉ እየተጋጠመና እየተያያዘ ራሱን በፍቅር ለማነጽ አካሉን ያሳድጋል።

ወዳጆች ነገሮች ጥሩ በማይሆኑበት ጊዜ ደህና እንደሆኑ በማስመሰል የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን እንደአካል ማነጽ አንችልም። እዉነቱን በፍቅር መናገር ይኖርብናል። በዚህ መልክ ነዉ ማደግ የምንችለዉ።

በቁጥር 3 ላይ የክርስትና ሕይወት ጉዞ በሠላም ጥምረት የመንፈስ አንድነትን እንደሚጠብቅ እናያለን።

**ሀ. አንድነት ከእግዚአብሔር መንፈስ ብቻ ነዉ መምጣት የሚችለዉ**

**ለ. የሠላም ጥምረትን መጠበቅ የምንችለዉ እርስ በርሳችን በመዋደድና እዉነትን በፍቅር በመናገር ነዉ**

ስለተጋቢዎች የጋብቻ ቀን የሰጠሁትን ምሳሌ ታስታዉሳላችሁ አይደለም? የሙሽሮቹ ቤተሰብ 45 ደቂቃ ዘግይተዉ ሲመጡ የሙሽሮቹ ቤተሰብ ደግሞ 45 ደቂቃ ቀድመዉ እንደመጡ ነዉ። ይሄ ክስተት አዲስ ለሚጋቡት ባልና ሚስት የግጭት ምክኒያት ይሆናል ብላችሁ ታስባላችሁ? አዎን ይሆናል።

ወዳጆች ልክ እንደነዚህ ተጋቢዎች እንዳንዳችን በዚህ ዓይነቱ የቃል ኪዳን ትስስር ዉስጥ እንገኛለን። ከዚህም የተነሳ ከሁለት አንዳችን በምንጎዳበት ጊዜ እዉነትን በፍቅር መናገር ይኖርብናል። ሆን ብየም ሆነ ባለማወቅ ቸር ሆኜ ባለመገኘቴ ባሳዝንህ እባካችሁ ወደእኔ ና። እዉነቱንም በፍቅር ንገረኝ። ይህን እንድናደርግ ነዉ እግዚአብሔር የጠራን። ይህን እፈልገዋለሁ።

ነገር ግን ይሄ እንዴት ሊሆን ይችላል? ለአንድነታችን ጠንካራ የሆነ መሠረት ሊኖረን ይገባል። ይሄ ደግሞ ወደሁለተኛዉ ነጥብ ይወስደናል።

## 11. የሕብረታችን መሠረት (ቁጥር 4-6)

እዚህ ላይ ስንቶችን ቆጠራችሁ? ሰባቶቹን። ከነዚህ ሦስቱ ለሥላሴዎች የሚሠሩ ናቸዉ፣ የተቀሩት አራቱ ደግሞ ከሥላሴ አካላት እንደስጦታ የተለገሰን የክርስትና ሕይወት ነዉ። እነዚህ ድግግሞሽን በዝርዝር እንመልከት።

### 1. አንድ አካል

ለአካል በደንብ እንዲሠራ ብልቶች በደንብ ሊሠሩ ይገባል። እኔ ያደግኩት በርካታ የእሳተ ገሞራ ክስተቶች ባሉበት ከተማ ነዉ። ጎማ የሚባለዉ የትዉልድ ቡታዮ ድንጋያማ ነዉ።
ርካስ ጫማዎችን መግዛት አንችልም ። 15 ዓመት ሲሞላኝ በከባድ ሁኔታ ወደቅሁ ይህም የግራ ጉልበቴን ጎዳኝ። በሥርዓት መራመድ አልቻልኩም፡ ስለጉልበቴ ሃሳብ ገባኝ፣ መቼም ድኜ እንደሚሻለኝ ያሳስበኝ ነበር። ግራ ተጋባሁ። ምንም እንኳን መላ ሰዉነቴ እግር ባይሆንም መላ ሰዉነቴ የችግሩ ተጋሪ ነበር።

ወዳጆቼ እኛ የክርስቶስ አካል ነን። አንዳችን በምንጎዳበት ጊዜ ከእነርሱ ጋር እንሰቃያለን እንወዳቸዋለን እንፀልይላቸዋለን። ሁላችንም አንድ አካል ነን። እኔና እናንተ በእግዚአብሔር ሕንጻ ዉስጥ ሸክላዎች ነን። በክርስቶስ አካል ዉስጥ አንድነትና ልዩነት ይኖራል። አንድ ድምጽ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ነዉ። ከአምስት አህጉራት የተዉጣጡ አባላት አሉን። ጳዉሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ

12፡12-31 ላይ እየተናገረ ያለዉን እንመልከት (በቁጥር 12-14 እና በ26 ኛዉ ቁጥር ላይ በማተኮር)

**1 ቆሮንቶስ 12: 12-14**

12 አካልም አንድ እንደሆነ ብዙም ብልቶች እንዳሉበት ነገር ግን የአካል ብልት ብልቶች ሁሉ ብዙዎች ሳሉ አንድ አካል እንደሆኑ ክርስቶስ ደግሞ እንዲሁ ነዉ። 13 አይሁድ ብንሆን የግሪክ ሰዎችም ብንሆን ባሪዎችም ብንሆን ባሪያዎችም ብንሆን፣ ጨዋችም ብንሆን እኛ ሁላችን በአንድ መንፈስ አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናልና። ሁላችንም አንዱን መንፈስ ጠጥተናል። 14 አካል ብዙ ብልቶች እንጂ አንድ ብልት አይደለምና።

**1 ቆሮንቶስ 12: 26**

26 አንድም ብልት ቢሣቃይ ብልቶች ሁሉ ከእርሱ ጋር ይሠቃያሉ። አንድ ብልትም ቢከበር ብልቶች ሁሉ ከእርሱ ጋር ደስ ይላቸዋል።

ክርስቶስ ሁላችንም ከርሱ ጋርና እርስ በርሳችን አጣምሮናል። ያሉን ልዩነቶች እንኳን እግዚአብሔር የሰጠን ልዩነቶች ናቸዉ። የጠብ ምክኒያት መሆን የለባቸዉም። ነገር ግን ከዚያ ይልቅ የእግዚአብሔርን በጎነትና ክብር እንድናከብር ያደርገናል።

## 2. አንድ መንፈስ

ሁላችንም በተመሳሳዩና በአንዱ የእግዞአብሔር መንፈስ ሕይወት ታድሎናል።
ምሳሌ፡ አሁን መንፈስ "ኑማ" የሚለዉ ቃል ለሕይወት አስፈላጊ እንደሆነዉ አየር ሊተረጎም ይችላል። ሁላችንም አንዱን አየር ነዉ የምንተነፍሰዉ። ወንድም ካሺል በአሜሪካ የፓኪስታኑን አየር ነዉ ወይ ትተነፍሳለህ ወይ? አንተስ ወንድም ዮቪ? በአሜሪካ ሆነህ የቶጎዉን አየር ትተነፍሳለህ ወይ? በርግጥ አይሆንም። እኛ የተለያየ ሣምባ አለን። ነገር ግን ሁላችንም ተመሳሳዩን አየር ነዉ የምንተነፍሰዉ። እኛ ሁላችንም ከተለያያ አገር የመጣን ክርስቲያኖች ነን። ምክኒያቱም እግዚአብሔር ለሁላችን በአንዱ መንፈስ ሕይወትን ሰጥቶናል።

አንድ መንፈስ ያለን ከመሆኑ የተነሳ እንደክርስቶስ አካል በአንድነት እንኖራለን።

## 3. አንድ ተስፋ

ሁላችንም አንዱን ተስፋ አንጋራለን። በክርስቶስ የሚያምን ማንኛዉም ሰዉ የዘላለም ሕይወት ይኖረዋል። ይሄ ተስፋችን ነዉ፡እንደዚሁም ለዘላለም ሕይወት በምንዘጋጅበት ጊዜ ያንን በዚህ መለማመድ አለብን። ስለአንድ ድምጽ ሕብረት እግዚአብሔርን እናመሰግናለን። አንድ ቀን ከክርስቶስ ጋር እንሆናለን በእግዚአብሔርም ሕልዉና ፊት ስለፍጹም አንድነታችን  በደስታ እንሞላለን። ያ ትልቅ ተስፋ ይሰጠኛል።

## 4. አንድ ጌታ

ሁላችንም የምናገለግለዉ አንድና ተመሳሳይ ጌታ አለን። ስለዚህ ለምንድነዉ የምንፎካከረዉ ወይም እርስ በርሳችን የምንጣላዉ? በጥንቷ የሮማ ዓለም ክርስቲያኖች የተጠሉ ነበሩ። ምክኒያቱም ከቄሳር ይልቅ ሌላ ጌታ እንዳላቸዉ ይናገሩ ነበርና። ቄሳር ጌታቸዉ መቀበል እስከቻሉ ድረስ ክርስቶስም ጌታቸዉ ሊሆን እንደሚችል እንደሚፈቀድላቸዉ ነዉ።
ነገር ግን ቄሳርና ኢየሱስ የተለያዩ መንግስታትን የሚስተዳድሩ ሁለት የተለያዩ ጌቶች ነበሩ። ነገር ግን ሁላችንም አንድ ያደረገን አንድና ተመሳሳይ የሆነ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አለን።

ፈረንሳዉያን "ላ ዩኒየን ፌት ላ ፎርስ " በሚል አነጋገራቸዉ በቀጥታ ሲተረጎም  "አንድነት ጥንካሬን ያመጣል" የሚል ሃሳብ አለዉ። መጽሐፍ ቅዱስም እንደዚሁ ይህን ሃሳብ ያስተጋባል። ከአንድ ሁለት ይሻላል(መክብብ 4፡9-12)። እኛ አንድ ጌታ ያለን ከመሆኑ የተነሳ አንድነትን ልንጠብቅ ተጠርተናል። ጥሩዉ ነገር እግዚአብሔር እንድናደርግ ለሚጠብቅብን ነገር እንፈጽመዉ ዘንድ አቅም ይሰጠናል። ስለዚህ ብርታትን ለመቀዳጀት እንፀልይ።

## 5. አንድ እምነት

በዚህ ያለነዉ ክርስቶስ ኢየሱስን እንደግል አዳኛችንና ጌታችን በማመናችን ነዉ። ክርስቶስን እንደግል አዳኝህና ጌታህ ካልተቀበልክ ይሄ ለአንተ ኃጢአትህን ለመናዘዝና ሕይወትህን ለጌታ ኢየሱስ ለማስረከብና እርሱን ብቻ እንድታምን የተሰጠህ ዕድል ነዉ።

አንድም ሰዉ ደህንነትን ለመቀዳጀት በርትቶ መሥራት አይችልም። ሁላችንም መዳን የቻልነዉ በእምነት በሆነዉ በፀጋ እንጂ እኛ በፈጸምነዉ የትኛዉም ሥራ አይደለም። ይሄንን ማወቅ ራሳችንን እንድናዋርድና በዓለም ዙሪያ ካሉት አማኞች ጋር ለአብሮነት ኑሮ ጥሪ ያቀርብልናል። ለወንጌል ምላሽ ስንሰጥ እርስ በርሳችን እንድንቀባበል፣ በአምልኳችን ደስተኛ እንድሆን፣ በክርስቶስ ያላቸዉን እምነት እንዲያዉቁና እንዲለማመዱት ጥሪ ያቀርባል(ሮሜ 15፡5-7)። ይሄ ፀጋ የጠፉትን እንድንወድ ይገፋፋናል። ምክኒያቱም እኛም የጠፋን ሰዎች ነበርን።

## 6. አንድ ጥምቀት

ሁላችንም በክርስቶስ ደም ታጥበናል። ይህም የአንድነታችን መሠረት ነዉ። የጥምቀት ሥርዓት ዛሬ ተግባራዊ የሚሆነዉ እኛ ዳግም የተወለድን ለመሆኑ ማሳያ ስለሆነ ነዉ(ዮሐ.3)። ለቃል ኪዳን ልጆችም እግዚአብሔር የሰጠዉ የአንድነት ምልክት ነዉ። ይሄንን ምልክት የሚጋሩት አዳኛቸዉና ጌታቸዉ በሆነዉ ክርስቶስ አማካኝነት መጣመር ይኖርባቸዋል።

## 7. የሁሉም ጌታና አባት የሆነዉ፣ ፣ የሁሉም የበላይ፣ በሁልም ዉስጥና በሁሉም ላይ ያለዉ።

አምላካችንና አባታችን ፍጹምና ሉዓላዊ ገዥ ነዉ። በምድር ሁሉ ላይ ክብሩን እናያለን(መዝ. 19)። ሁሉንም ሲገዛ ማየት እንችላለን። መፍራት የለብንም። ለሚያስፈልገን ነገር ሁሉ በእርሱ ላይ እንታመናለን። ትዕግስት ከማጣትና እርስ በርሳችን ከመናቆር   ጭንቀታችንን በእርሱ ላይ

እንጥላለን(1ጴጥ. 5፡7)፡፡ ይህንን በምናደርግበት ጊዜ ሁሉም በእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር መሆኑን መቀበላችን ነዉ፡፡ ትዕግስት ስናጣ በሁኔታዎቻችን ወይም በጓደኛዎቻችን ላይ የበላይና ሉዓላዊ ለመሆን መጣራችን ነዉ፡፡ ሆኖም በነገሮች ሁሉ ላይ የበላይ ነዉ፡፡ ሁሉንም ተቆጣጥሮታል፡፡ እንደአንድነታችን እዉነተኛ መሠረት በእርሱ እንታመናለን፡፡

ምሳሌ፡ የአንድ አባት ልጅ መሆን ምን ማለት እንደሆነ አሁን አዉቀናል፡፡ ልጆች የተለያዩ ናቸዉ፡፡ የተለያዩ ነገሮች ይፈልጋሉ፡፡ ነገር ግን በአንድ የጋራ የሆነ እምነት አማካኝነት መጣመር አንድነታቸዉን ያጠናክራል፡፡ እንደክርስቲያን አንድነታችን በሰማዊ አባታችን ላይ ተመሥርቷል፡፡ ከዚህም የተነሳ አንድነታችን በጣም የተጠናከረ ነዉ፡፡

አባታችን ከሁሉም በላይ በመሆኑ አንድነታችንን ለመጠበቅ በልጁ በክርስቶስ በኩል የሚያስፈልገንን ስጦታ ችሮናል፡፡ ይህ ነዉ ታዲያ የሚቀጥለዉ ነጥባችን፡፡

# 111. የአንድነታችን ስጦታ (ቁጥር 7-8)

## ክርስቶስ የአንድነታችንን ስጦታ አበርክቶልናል፡፡

ቁጥር 8 ከመዝሙር 68፡18 የተወሰደ ጥቅስ ነዉ፡፡ ክፍሉም የሚያሳየዉ አንድ የጦር አበጋዝ በጠላቶቹ ላይ ድልን ከተቀዳጀ በኋላ ጠላቶቹን ምርኮኛ እንዳደረጋቸዉ ነዉ፡፡ እናም ኢየሱስ ክርስቶስ ምርኮኞችን በድል የመራ ነዉ፡፡ እናንተና እኔ የርሱ ድል ዋንጫዎች ነን ፡፡

ምሳሌዎች፡ በልጅነቴ የእግር ኳስ ተጫዉቻለሁ፡፡ አንዳንድ ጊዜ የፊፋ የአለም ዋንጫን መመልከት ያስደስተኛል፡፡ የማጠናቀቂያዉ ክፍለ ጊዜ ሁልጊዜ ለማየት የሚያጓጓ ነዉ፡፡ ዋንጫዉ ለአሸናፊዉ ቡድን ሲሰጥ ማየት በተለይ በጣም የሚያጓጓ ነዉ፡፡

አሁን ኢየሱስ ጫወታዉን ብቻ አይደለም ያሸነፈዉ፡፡ ለነፍስህ ሲል ጦርነቱን ድል ማድረጉ ነዉ፡፡ እኛ የድሉ ዋንጫዎች ነን፡፡ ከኃጢአት ባርነት እኛን ነፃ ለማዉጣት በሚያሳምምና በመከራ ዉስጥ አልፏል፡፡ ይህም የዘላለም ሕይወት እንዲኖረን እንዳንጠፋ ከማሰብ አንፃር ነዉ(ዮሐንስ 3፡ 16)፡፡

ለኃጢአት ባሪያዎች ከመሆን የክርስቶስ ባሪያዎች ለመሆን የዳንን ሰዎች ነን፡፡ ኢየሱስ መልካም ጌታ ከመሆኑ በስተቀር ፡፡ ክርስቶስ አካሉ ያድግ ዘንድ ከአገልግሎት ስጦታ ጋር መንፈስ ቅዱስን በቤተ ክርስቲያን ላይ አፍስሷል፡፡ እንድናገለግለዉ ይፈልጋል፡፡ ያለእርሱ በስተቀር ልናገለግለዉ እንደማንችል እርሱም ያዉቃል፡፡ በመሆኑም የሚያስፈልገንን ሰጥቶናል እነዚህንም በስም ስንጠቅሳቸዉ እርስ በርሳችን እንተናነጽ ዘንድ የሚያስፈልጉን መንፈስ ቅዱስና የፀጋ ስጦታዎች ናቸዉ፡፡ ለዚህም በረከቱን ሁሉ ለሚያፈስልን አምላክ ምስጋናን በማቅረብ ምላሻችንን ማሳየት ይኖርብናል፡፡

## ከቁጥር 7 እና 8 ላይ ክርስቶስ የፀጋ ልኬት መሆኑን እናስተዉላለን፡፡

የማይገባንን ሁሉ አግንተናል፡፡ ይህም የክርስቶስ የደህንነት ስጦታ ሁሉ ፍሬ ነዉ፡፡ እነዚህ ን ሁሉ ስጦታዎች ቤተ ክርስያኑን ለማነጽ ሰጥቶናል፡፡ ወዳጆች የፀጋ ስጦታዎች ለእግዚአብሔር ክብርን ያመጡለታል፡፡ በተጠናቀቀ ደረጃ ላይ አይደለም ያለነዉ፡፡ ነገር ግን አንድ ከሆነዉ ጌታ ጋር ነዉ ሁላችንም የምንሮጠዉ፡፡ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል አማካኝነት ከአንዱ ጌታ ጋር፡፡

በ1ኛ ቆሮ. 4፡7 ላይ እንዲህ የሚል ቃል እናነባለን፣

**1 ቆሮንቶስ 4፡ 7**

አንተ እንድትበልጥ ማን አድርጎሃል? ያልተቀበልከዉ ምን አለ? የተቀበልህ ከሆነ ደግሞ እንዳልተቀበለ የምትካዉ ስለምንድነዉ?

በክርስቶስ አማካኝነት አንድ ጌታ፣ አንድ መንፈስና አንድ ጥምቀት፣ አንድ እምነት፣ አንድ ተስፋና እንደአንድነታችን መሠረት አንድ አካል አለን፡፡ ጳዉሎስ ከክርስቶስ ጋር ካለን ሕብረት የተነሳ እንደአማኝ አንድነታችንን ከደህንነት ስጦታችኝ ነጥለን እንድናየዉ አይፈልግም፡፡ በተልእኮዉ ፍፃሜ ላይ ክርስቶስ ለሰዎች ሁሉ የሚሆነዉን ስጦታ አበርክቷል(ወንዶችና ሴቶች)፡፡

እያንዳንዳችን ስጦታዎች አሉን፡፡ ትልቅና ትንሽ የሚባል ስጦታ የለም፡፡ ለእኛ ተስማሚ መስሎ የታየዉን ስጦታ አድሎናል፡፡ መሰሉን ድርጊት እኛ መፈፀም አንችልም፡፡ ሆኖም የክርስቶስን አካል እናገለግላለን፡፡ ከዚህም የተነሳ በትህትና መንፈስና በትዕግስት አንዳችን ሌላዉን ማገልገል እንፈልጋለን፡፡ ይህ ነዉ ለክርስቶስ ክብርን የምናመጣበት መንገድ ፡፡

ምሳሌ፡ ቡድናችን የተለያዩ ስጦታዎች እንዴት አድርገዉ ጌታን እንደሚያከብር ጥሩ ምሳሌ ነዉ፡፡ እኔ እዘምራለሁ ጊታርም እጫወታለሁ፡፡ ነገር ግን ከበሮ መምታት አልችልም ፡፡ ብዘምርም ለምሳሌ እንደ ካሺፍ ዝቅ ባለ ድምጽ መዘመር አልችልም፡፡ እንደዚሁም በሴቶች ድምጽ መዘመር አልችልም ምክኒቱም ያ ለሴቶች የተሰጠ ድምጽ ነዉ፡፡ ነገር ግን እነዚህን ድምፆች ወደአንድነት በምናመጣበት ጊዜ በአንድነት በማክበራችን ደስታ ይሰማናል፡፡ ጌታ የሰጠን የተለያዩ ስጦታዎች በአንድነት በምናከብረዉ ጊዜ የበረከት የደስታ ምንጭ ይሆናሉ፡፡

## ማጠቃለያ

ልክ እንደጳዉሎስ በክርስትና ህይወት እርምጃችን እግዚአብሔርን ማስደሰት ይቻለን ዘንድ ለበለጠ ፀጋ እንፀልይ፡፡ ይህም በእዉነተኛ ፍቅርና አገልግሎት እርስ በርሳችን አንድነታችንና ሰላማችንን በማጠናከር ይሆናል፡፡ እንደአንድ ድምጽ አባላት የቤተ ክርስቲያኑን አንድነት ለመጠበቅ ጌታ ይርዳን፡፡

## እንፀልይ

አባት ሆይ ስለቃልህ እናመሰግንሃለን። ዳግም ልደት ባገኘንበት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል አማካኝነት ከክርስቶስ ስላገኘነዉ የደህንነት ስጦታ እናመስግንሃለን። በዉሃ ጥምቀት አማካኝነት ወደህይወት ስለመጣኸን እናመሰግንሃለን። ለእኛ ያደረከዉን ነገር በምናስብበት ጊዜ ያንን የሚመጥን ነገር ለማሰብና ለማድረግ እንድንችል እርዳን። ለጥሪህ ምላሽ ስንሰጥ በትህትና፣ በጭምትነት፣ በትዕግስትና በመቻቻል መንፈስ ለመራመድ እንድንችል አቅም ሁነን። በአምልኳችን ደስተኞች እንድንሆንና ከጎረቤቶቻችን ማህበረሰብ በመጀመር ዓለምን በወንጌል ለመድረስ ችሎታን አላብሰን። ትልቁ ግባችን በአንድ ላይ ሆነን ዘላለማችንን እያስደሰትንህ ክብርን ለአንተ ማቅረብ ይሁን። ይህን ሁሉ በኢየሱስ ስም እንፀልያለን። አሜን!